# የታካሚ መረጃ፦ ፓክስሎቪድ (PAXLOVID)



ፓክስሎቪድ (PAXLOVID) በ COVID-19 ለሚመጣ ከባድ ሕመም በከፍተኛ ደረጃ ተጋላጭ ለሆኑ ጎልማሶች በሆስፒታል መተኛትን ወይም ሞትን ሊከላከል ይችላል። የ COVID-19 ምልክቶች መታየት በጀመሩ በ5 ቀናት ውስጥ መወሰድ አለበት።

## ፓክስሎቪድ (PAXLOVID) ምንድን ነው?

**ፓክስሎቪድ (PAXLOVID) አዲስ መድኃኒት ሲሆን ከቀላል እስከ መካከለኛ COVID-19 ን በሚከተሉት ሰዎች ላይ ለማከም ያገለግላል፦**

- ዕድሜአቸው 12 ዓመትና ከዚያ በላይ ሆኖ ቢያንስ 88 ፖውንድ የሚመዝኑ
- የ COVID-19 ቫይራል ምርመራ ፖዘቲቭ የምርመራ ውጤት ያላቸው
- በሆስፒታል *መተኛትን እና ሞትን ጨምሮ ለከባድ የ COVID-19 ህመም*ከፍተኛ ተጋላጭነት ያላቸው

**ፓክስሎቪድ (PAXLOVID)** ለ 5 ቀናት በአፍ (እንክብሎችን በመዋጥ) የሚወሰድ ፀረ-ቫይረስ መድሃኒት ነው። የህመም ምልክቶች መቀነስ ቢያሳዩም እንኳን፣ የሕክምናው ሂደት (መድሃኒቱን መውሰዱ) መጠናቀቅ አለበት።

የአሜሪካ የምግብ እና የመድኃኒት አስተዳደር (FDA) **ፓክስሎቪድ (PAXLOVID)** በ COVID-19 ወረርሽኝ ወቅት እንዲገኝ ለማድረግ የአደጋ ጊዜ አጠቃቀም ፈቃድን (EUA) ሰጥቷል። ፓክስሎቪድ (PAXLOVID) በዩናይትድ ስቴትስ ውስጥ በ FDA የጸደቀ  መድሃኒት አይደለም።



## የሚከተሉት ሁኔታዎች ካሉብዎት ለጤና እንክብካቤ አቅራቢዎ ይናገሩ፦

- የትኞቹም አይነት አለርጂዎች ካሉብዎት
- የኩላሊት ወይም የጉበት በሽታ ካለብዎት
- ነፍሰ ጡር ከሆኑ፣ ወደፊት ነፍሰ ጡር ሊሆኑ የሚችሉ ከሆነ
- ልጅ እያጠቡ ከሆነ
- የትኞቹም አይነት ከባድ ህመሞች ካሉብዎት
- መድሃኒቶችን እየወሰዱ ከሆነ (በሃኪም የታዘዙ፣ ካለማዘዣ የሚዋሰዷቸው፣ ቫይታሚኖች ወይም የእፅዋት ውጤቶች)
- ድብልቅ የሆርሞን የወሊድ መከላከያዎችን እየወሰዱ ከሆነ (ፓክስሎቪድ (PAXLOVID) በወሊድ መከላከያ ክኒኖችዎ አሰራር ላይ ተፅዕኖ ሊያስከትል ይችላል)

## ፓክስሎቪድ (PAXLOVID) የጎንዮሽ ጉዳቶች አሉት?

- **ፓክስሎቪድ (PAXLOVID)** ከሚወሰዷቸው ሌሎች መድሃኒቶች ጋር መስተጋብር ሊፈጥር ይችላል።  ስለ ሁሉም አሁን ስለሚዋሰዷቸው መድሃኒቶችዎ ለሐኪምዎ መናገር አስፈላጊ ነው።
- **ፓክስሎቪድ (PAXLOVID)** የጉበት ችግሮችን **ሊያመጣ ይችላል።**
- **ፓክስሎቪድ (PAXLOVID)** በኤች አይ ቪ መድሃኒቶች ላይ **የመቋቋም ሁኔታ መፈጠርን** ሊያስከትል ይችላል።
- ሌሎች **የጎንዮሽ ጉዳቶች** የሚከተሉትን ያካትታሉ፦
  - የተለወጠ የመቅመስ ስሜት
  - ተቅማጥ
  - ከፍተኛ የደም ግፊት
  - የጡንቻ ህመሞች





## ፓክስሎቪድን (PAXLOVID) የት ማግኘት እችላለሁ?

**የፓክስሎቪድ (PAXLOVID) መገኛ ቦታዎች በ VDH የ COVID-19 ሕክምና ጠቋሚ መሳሪያ ላይ ይገኛሉ። ሊንኩ በቨርጂኒያ ውስጥ ህብረተሰቡ እና አቅራቢዎች የህክምና ጣቢያዎችን ወይም ቦታዎችን እንዲያገኙ የሚያስችል በ VDH ድረ-ገጽ ላይ በድረ-ገጽ የተሳሰረ ካርታ (interactive map) ነው፦**
*https://www.vdh.virginia.gov/mabs/covid-19-treatment-locator/*

**ለሁሉም ሊገኙ ለሚችሉ መፈውሦች/ሕክምናዎች የሐኪም ማዘዣ ያስፈልጋል።**

VIRGINIA'S HEALTH IS IN OUR HANDS.
Do your part, stop the spread.

ስለ COVID-19 ሕክምናዎች ተጨማሪ መረጃ በ *https://www.vdh.virginia.gov/coronavirus ላይ ማግኘት ይችላሉ።*

VDH VIRGINIA DEPARTMENT OF HEALTH